የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

| አሥራ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፴፭<br>አዲስ አበባ ሰኔ ፩ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም | በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ<br>የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | 18th Year No. 35<br>ADDIS ABABA 8th June, 2012 |
|---|---|---|

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፯፻፵፭/፪ሺ፬ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በኮሪያ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የተደረገው የሳይንስና ቴክኖሎጂ ትብብር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ …... ገጽ ፮ሺ፫፻፵፰

CONTENTS

**Proclamation No.745/2012**

Agreement on Scientific and Technological Cooperation between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Korea Ratification Proclamation. ... Page 6348

## አዋጅ ቁጥር ፯፻፵፭/፪ሺ፬

### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በኮሪያ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የተደረገውን የሳይንስና ቴክኖሎጂ ትብብር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኮሪያ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የሳይንስና ቴክኖሎጂ ትብብር ስምምነት ሐምሌ ፩ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፱ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በኮሪያ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የተደረገው የሳይንስና ቴክኖሎጂ ትብብር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፯፻፵፭/፪ሺ፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION No. 745/2012.

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT ON SCIENTIFIC AND TECHNOLOGICAL COOPERATION BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE REPUBLIC OF KOREA

WHEREAS, the Agreement on Scientific and Technological Cooperation between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Korea was signed in Addis Ababa, on the 8th day of July 2011;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 17th day of May, 2012;

NOW, THEREFORE, in accordance with sub-article (1) and (12) of Article 55 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Agreement on Scientific and Technological Cooperation between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Korea Ratification Proclamation No.745/2012".

## ፪. የስምምነቱ መጽደቅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በኮሪያ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል ሐምሌ ፩ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የሳይንስና ቴክኖሎጂ ትብብር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

## ፫. የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ሥልጣን

የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር አግባብ ካላቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመተባበር ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ የሚያስፈልጉ እርምጃዎችን የመውሰድ ስልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

## ፬. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሰኔ ፩ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም**

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ

ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

## 2. Ratification of the Agreement

The Agreement on Scientific and Technological Cooperation between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Korea signed in Addis Ababa on the 8th day of July, 2011 is hereby ratified.

## 3. Power of the Ministry of Science and Technology

The Ministry of Science and Technology is hereby empowered to undertake, in cooperation with the concerned governmental organs, all acts necessary for the implementation of the Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 8th day of June, 2012.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL**

**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**